# ይድረስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት

***ኤልሳዕ ከኤልያስ የተረከበውን አጽፍ በደስታ እንደለበሰው፤ ከሊቃውንት አባቶቻችን የተረከብነውን አጽፍ ለብሰነዋል ወይስ ጠቅልለን ለቀበኛ ላም አጉርሰነዋል?***

የተከበራችሁ የኢትዮጵያውያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሆይ! ከሁሉ አስቀድሜ የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ:: ከደብዳቤ ይልቅ በአካል ተገናኝተን በብዙ አቅጣጫ በመጎዳት ላይ ስላለችው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ጠቃሚ ነገሮችን ብንወያይ እጅግ መልካም በሆነ ነበር:: ወደፊት ይህ እዲሆን እመኛለሁ፥ አምናለሁም:: ይህ ደብዳቤ በታሪክ አጋጣሚ በቅርቡ እዚህ አሜሪካን አገር የመጡትን አቡነ ቀውስጦስን መነሻ አርጎ ይጻፍ እንጅ በአገራችን በገዳማት፥ በዱሩ፥ በገደሉ፥ በገጠር፥ በከተማው ደበሎና ድሪቶ ለብሰው ሽምብራ ቆሎ እየቆረጠሙም ሆነ በተዋበ ካባ ተሽሞንሙነው ጮማ እየቆረጡ የሚኖሩትን ሊቃውንት ሁሉ ይመለከታል:: ደብዳቤው በመጀመርያ ሙሉ በሙሉ የተጻፈው ቅዱሳን የቤተክርስቲያን አባቶቻችን ከጥንት ጀምሮ ስለ አፈጣጠርና ስለ ፍጥረታት በሚፈላሰፉበት የግእዝ ቋንቋዋ ነበር:: ነገር ግን መላውን የአገራችንን ሕዝብ ለማካፈል ሲባል መልእክቱ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ቀርቡዋል::

ዳዊት ከተወለደበትና ከጓደኞቹ ጋር ውሀ እየተራጨ ካደገባት ከቤተ ልሔም ምንጭ ርቆ በቆየበት ዘመን፥ ጓደኞቹና ምንጭት ትዝ ብለውት "ከዚያች ምንጭ ውሀ ማን ባመጣልኝ" እንዳለው የአቡነ ቀውስጦስ መምጣት ቅዱሳት መጻሕፍትን እየተመገብን ባደግንባት በዚያች ቅድስት ጉባዔ ቤታችን ያሳለፍነውን መከራም ሆነ ደስታ አስታወሰኝና ቤተክርስቲያናችን የገባችበት መቀመቅ አንገቴን አስደፍቶ እነደማያስተክዘኝ ሁሉ ደስ አለኝ:: እርቄ በኖርኩበት ዘመን ስለአገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን የሚሰሙና የሚነገሩ ብዙ ነገሮች አሉ:: ታዲያ እንደምሰማው ከሆነ መምሕሮቻችንም አልቀው የጉባዔ ጓደኞቻችንም ተበታትነው ባሉበት በዚህ ወቅት ወደ አገር ቤት ብመለስም እውነቱን ለማወቅ ከርሳቸው የተሻለ የሚነግረኝ የማገኝ አልመስል አለኝ:: ስለዚህ የርሳቸው ወደኛ መምጣት ስለገዳማቱ፥ አድባራቱ ሊቃውንቱና ጠቅላላ ምእመናኑ በእምሮየ ለሚመላለሰው ጥያቄየ በመጡኑም ቢሆን ሊአረካ የሚችል መልስ አገኛለሁ ብየ እንድገምት ገፋፋኝ::

ወደ ጥያቄየ ከመሻገሬ በፊት አደራውን ስላስረከቡን ቅዱሳን ሊቃውንት አባቶቻችንና፥ እንዴት እንዳስረከቡን ለጥቂት ደቂቃወች ብናወሳ የራሳችንን ድካም እንድናይ አይናችንን ይከፍትልናል ብየ አስባለሁ:: ችግራችንን እና መፍትሔውንም እንድንገነዘብ የሚረዳን ይመስለኛል:: በዚያች ቅድስት ጉባዔ ቤታችን ከነበርነው ሁሉ በእውቀትም በእድሜም የመጨረሻው ብሆንም በዚያን ጊዜ ስለትምሕርት ቤቱና በኛ ላይ ተጥሎብን ስለነበረው ተስፋ ሲነገር የሰማሁትን በግልጽ አስታውሳለሁ:: ነብያት ባካባቢያቸው ለሚፈጠረው ችግር ካካባቢው መልስ ሲአጡ *«ሰማይ ስሚ ምድርም አድምጭ»* ብለው ንግግራቸውን ከቆሙበት ቦታ እንደሚጀምሩ እኔም ሓሳቤንም ሆነ ጥያቄየን ኃላፊነት ከተረከብንባት ከተቀደሰችው ቦታ ከጉባዔ ቤታችን ልጀምረው ወደድኩ:: እንግዲህ ከተሳሳትኩ አርሙኝ:: ያች ጉባዔ ቤታችን የተመሠረተችው ጣሊያን አገራችንን ባፈረሰበት አብያተ ክርስቲያናትን ባቃጠለበት ዘመን፥ እንኳን ሰው ምድሪቱም አትገዛልህም፥እኛም ወደ ካቶሊክ እምነትም አንቀየርም በለው ከጀግኖች ጋር ሆነው በመዋጋት ያለቁትን ሊቃውንት አባቶቻችንን ለማስታወስና እነሱን ለመተካት በነ መምሕር ገብረ ኢየሱስ ስም ንጉሡና በዘመኑ የነበሩት ፓትርያክር አቡነ ባስልዮስ በደብረ ሊባኖስ መሠረቱት::

ከዚያም የታወቁትንና ምርጥ የተባሉትን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሊቃውንት ሰበሰቡ፥ እኛንም ከአገሪቱ አብነት ትምህርት ቤቶች ሰብስበው፥ የሊቃውንቱን ጉባዔ ከፍተኛ ትምህርት ለመቀበል የሚአስችለንን ቅኔውንና የግእዙን ያተረጓጎም ስልት የሚረዳውን የመግቢያ ፈተና በሊቃውንት ጉባዔ ፈትነው ወደ ደብረ ሊባኖስ ሲልኩን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስና ምክትል ፓትርያርኩ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የነገሩን የማይሞት የአደራ ቃል እንደዚህ የሚል ነበር:: "ወዴት እንደምንልካችሁ ታውቃላችሁ? የምትሔዱበትስ የመጨረሻው ደረጃ ትምህርት የሚሰጥበት ጉባዔ ቤት ለምንና በማን ስም እንደተሠራ ታውቃላችሁ" እያሉ አዕምሮአችንን ከቀሰቀሱ በኋላ *"ሂጂ አገርሽ ግቢ ተመለሽ ቅኔ፥ ወንዶች በዋሉበት መዋሌ ነው እኔ"* እያሉ ሊቅነትን ታማኝነትን: ወሳኝነትን እውነትን ጀግንነትን ታጥቀው ለአገራቸውና ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸው ከጣሊያን ጋራ በመተናነቅ የወደቁትን ሊቃውንት ለማስታወስ እና እነሱንም ለመተካት በነ መምሕር ገብረ ኢየሱስ ስም ወደ ተመሠረተው ጉባዔ ቤት ነው የምንልካችሁ:: እስካሁን የተማራችሁት ቅኔ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመመርመርና የግእዙን ቋንቋ ለማብሰል በቂ አይደለም:: የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ስልት ከታወቁት ሊቃውንት ካልተማራችሁበት ቅኔ ብቻውን ዘርቀኛ፥ ተረበኛ፥ ትዕቢተኛ፥ ፌዘኛና፥ ቀልደኛ ዋዘኛ አድርጎ አዕምሮአችሁን ያቀጭጨዋል እንጅ አያሰፋውም:: ከጉባዔ ቤቱ ተሰብስበው ከሚጠብቋችሁ ሊቃውንት አባቶቻችሁ በፊታችሁ የሚአፈሱትን አንድምታ ፈጽማችሁ ከወጣችሁ፥ ሁልጊዜ ትኩስና የተዘጋጀ ምጣድ ትሆናላችሁ:: ለግል ጥቅማችሁ ለመቆም የምታፍሩ ትሆናላችሁ:: ለእውነት፥ ለእምነት ለወገን ለመቆም ደፋሮች ትሆናላችሁ፥ ወደፊት የምትኖሩባት ዓለም እያመነጨች ለምታቀርባቸው አዳዲስ ነገሮች በርጋጊዎች ከመሆን ይልቅ ተርጓሚወች ትሆናላችሁ፥ ስለሰው ልጅ ብቻ አይደለም፥ ከዚያም አልፋችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁ ባካባቢያዋ የበቀሉት ሁሉ ዕጸዋት እንዳይቆረጡ ያወገዘችበትን ሁሉ ምሥጢር ትረዳላችሁ" አሉን::

አባታዊ ምክራቸው በዚህ አላበቃም:: አቡነ ቴዎፍሎስ ቀጠሉና «በተለይ ልጅነት ያላችሁ የምትሄድሉትን የቤታችን

የጉባዔ ትምህርት ከፈጸማችሁ በኋላ በዘመኑ ትምህርት እንድትገቡበት ተዘጋጁ:: የታወቀው የአንጾኪያው ኦርቶዶክሳዊው ዮሐንስ በዘመኑ ለነበረው እውቀት እንግዳ ባለመሆኑ "*ዘተዋሕዶ አሰፈውናሁ ከመ ንሕነ ንግበር ዘንተ ወሐለየ ከመ ዘኢንክል ንሕነ ዘንተ ወኢነአምር ዋጸሐፈ ስምዐተ ዘዘከርናሆሙ በተፍጻሜተ ዝንቱ ማጽሐፍ በጽርዕ ወአብጻሕናሃ ወመጠውናሃ ሎቱ ወሶበ ነጸረ ውእቱ ዘውስቴታ አቀመ ታጤይቁነኑ እምነገረ ቅዱስ ቄርሎስ ስምዐ ዝወኢያንበባ* (ሃኰ አበው ም ፻፪: እንዳለው፥ እናንተም እንደሱ ትሆኑ ዘንድ ሐረር ወደ ተከፈተው አዳሪ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ሰዋስዎ ብርሃን ትሄዳላችሁ» አሉን:: ደብረ ሊባኖስ ከሄድን በኋላም የሚቆየንን ፈተና እንዲህ ብለው አስጠንቅቀውን ነበር:: «ገና ጫጋልን ስትወርዱ የምታይዋቸው ወጣት መነኮሳት ናቸው:: እነሱ የመነኮሱት የመንግሥተ ሰማያትን ጣእም የገሀነምን ምሬት ለይተው አውቀውት አይደለም:: የነእንጦስንና የነመቃርስን ሕይወት አንብበው ገብቷቸው አይደለም:: ካካባቢው የገለበጡት ነው:: እናንተ ግን ገልባጮች እንዳትሆኑ፤ ምንኩስናውን አጥኑት እንጅ አትግቡበት:: በግልበጣ የሚፈጸም ምንኩስና አይጥና ወፍ ሆና ራሷን ያጣች የሌት ወፍ ያደርጋል እንጅ እንደ እነእንጦስ አያደርግም:: እናንተን ወደ ደብረ ሊባኖስ የምንልካችሁ መንኩሳችሁ በዚያው እንድትቀሩ አይደለም:: ከፊቷ በምታየው ቀለም ቀልቧን እንደምትጥል እስስት መንኩሰው የምታይዋቸውን ወጣት መነኮሳት በማየት የተላካችሁበትን ቁም ነገር ጥላችሁ እየመነኮሳችሁ እዚያው በመቅረት የቁራ መልክተኞች እንዳትሆኑ::» እያሉ የወጣቱን አምሮ ከምንኩስናው ይልቅ በሕግ ተወስነን ካህናት እንድንሆን ለትምህርትና ለትዳር ያዘጋጁን ነበር::

ደጋግመው ባንክሮ ሲመክሩንም "ብትመነኩሱ ግን አሁኑኑ እወቁት! ከገዳሙ እንድትወጡ አይፈቅድላችሁም:: የምንመኝላችሁ የተላካችሁበትን ትምህርት ከፈጽማችሁ በኋላ እድሜአችሁ የፈቀደላችሁ በሕግ ተወስናችሁ በየአድባራቱ በቤተ ክህነቱና በተፈለጋችሁበት በር ከፍቶት ከሚአለቅሰው ጋር እንድታለቅሱ፥ ከሕዝባችሁ ጋር በመኅራበት ከሕዝቡ ጎን እንድትሰለፉ ነው:: ራሳችሁ የምታውቁት በሽታ ያለባችሁ ለትዳር አቅምና ሙሉ ጤንነት የሚአንሳችሁ ደግሞ እራሳችሁን እየመረመራችሁ ቆቡን ለመድፋትና ተገንዘናል ሞተናል ብላችሁ በራሳችሁ ሞትን ለማወጅ ሳትቸኩሉ እዚያ በገዳማቱ ዙሪያ በመምህርነት ለመሰለፍ እራሳችሁን አዘጋጁ:: ለዘመኑ ትምህርት እድሜአችሁ የሚፈቅድላችሁ ግን ወደ ሰዋሰዎ ብርሃን መጥታችሁ እንድትቀጥሉ:: በጉባዔ ቤት የሚጠብቋችሁ ሊቃውንት ደብረ ሊባኖስ የገቡት መንነው አደለም:: ይህን ስንል፥ ከዓለምና ምኞቷ ሁሉ ተለይተን ተገንዘን ሞተናል (ወይም መንኩሰናል) ብለው በራሳቸው ሞትን አላወጁም እንጅ ይህችን ዓለም ንቀው የጎረጥ የሚያዩዋት በሥነ ባሕርያቸው ከፈጣሪያቸው መንበረ ፀባዖት የገቡ ሥጋ የለበሱ መላእክቶች ናቸውና ከነሱ የምትቀበሉት ትምህርቱን ብቻ ሳይሆን ምናኔአቸውን መንፈሳዊነታቸውን ሁሉ ነው" ብለው መክረውን ነበር::

ደብረ ሊባኖስ ስንደርስም የላኩን ቅዱሳን አበው እንደነገሩን ሆኖ ሁሉንም አገኘነው:: የሐዲሱ፥ የሊቁ፥ የብሉዩ፥ ሊቃውንት አባቶችም በዘመኑ በከፍተኛ መጠን ታስቦ ይከፈላቸው የነበረውን የወር ገቢና በዘመኑ መልክ የተደራጀላቸውን ኑሮ ከነሱ በፊት ከነበሩት መምህራን ኑሮ ጋር በማነጻጸር «እለ ብዙኃን ወጠኑ ይንግሩ ወይምሐሩ በእንተ ግብር ዘአምኑ በላእሌነ:: ሊተኒ ረትአኒ» እያሉ ደስ ብሏቸው ምሥጢረ መጻሕፍትን ይመግቡን ነበር:: በዚያች ጉባዔ ቤታችን ከከበብናቸው መደበኞች መምሕራኖቻችን ውጭ እነ የኔታ ፍስሐ ዘልቱት ልሳኑ (በጣሊያን ጥይት ምላሳቸውን እንደተጎዱ ይነገርላቸዋል) ከጉባዔ መምሕሮቻችን ያመለጠውን የመጻሕፍትን ምሥጢር እንደሐረግ እየመዘዙ በአዕምሮአችን ይስሉት ነበር:: የኔታ አምዴና የኔታ አንዳርጌም ከጉባያቱ የሰማናቸውንና የተማርናቸውን ከየኔታ ፍስሐም የተረዳናቸውን መሥጢራተ መጻሕፍት ከተረትና ዘርቅ በጠራው ቅኔአቸው መነጸር እንድን መለከተው ያኟሹን ነበር:: እነዚህ ሁሉ ሊቃውንት እነሱ ኤልያሶች እኛ ኤልሳዎች ሆነን ከነሱ የበለጠ እንድናደርግ ትልቅ ነገር ከኛ እንደሚጠብቁ ይነግሩን ነበር:: በዚያን ወቅት አበው ሊቃውንት በኛ ላይ የነበራቸው ተስፋ ነቢዩ ኤልያስ በደቀ መዝሙሩ በኤልሳዕ ላይ የነበረው አይነት ተስፋ ነበር:: ለምሳሌ ይጠቅሱልን  የነበረው የታሪክ ሰው ኤልሳዕ ቅኔአችንን ከዘርቅ ለማውጣት ከምንማረው ከመጽሐፈ ነገስት ፩ኛ ምእራፍ ፲፱ እስከ ፪ኛው ነገሥት ምእ ፫ ድረስ ሰፍሮ ያለው ነበር:: እኛ ከሊቃውንቱ አስተማሪዎቻችን ኃላፊነትንና ተስፋን የተረከብንበትን ስልትና መንገድ የበለጠ ለመገንዘብ ነቢዩ ኤልያስ ለተማሪው ለኤልሳዕ እንዴት እንዳስረከበው ለደቂቃ እንቃኘው::

ኤልያስ እንደመምሕሮቻችን የመንፈስ የእምነትና የተስፋ ሰው ነበር:: የሱን የመንፈስ ልዕልና የጠነከረ እምነት የሚረከብለት ደቀ መዝሙር በፍለጋ ላይ የነበረ ምድራዊ መላክ ነበር:: አራሹን ኤልሳዕን በበሬወቹ መካከል እንዳለ አሻግሮ ሲመለከተው አደራውን የማይረሳ ታማኝ ሰው ሆኖ በሚዛኑ ገባለት:: ኤልያስ የተሸከመውን አላፊነት ከራሱ ትክሻ ላይ አንስቶ በኤልሳዕ ትክሻ ላይ ለመጫን የተጠቀመው የለበሰውን የራሱን አጽፍ ከተከሻው ላይ አንስቶ በተማሪው በኤልሳዕ ትክሻ ላይ በመጫን ነበር:: ኤልሳዕም ኃላፊነቱ ወደሱ ሲመጣ ለጊዜው ተጨነቀ መንፈሱም ተሸበረ፥ ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ግን ኤልሳዕ የራሱ ሰው አልሆነም:: ወደ ኋላ ሊመለስ በማይችልበት ሁኔታም አደራውን ለመሸከም ራሱን አስተካከለ:: ሁሉንም አለማዊ ነገር አራግፎ ተወ:: ቤተሰቦቹን ተሰናበተ፥ ሕሊናውን የሚጎትተው አንድ ነገር እንዳይኖር በሱና በምድራዊ ዓለም መካከል የነበረውን ግንኙነት ሁሉ ተወ:: ከእርሻውም አፈሩን አራግፎ ወጣ:: ቀንበሩን ሞፈሩን፥ እርፉን የከሱ በሬዎቹን መስዋት አድርጎ አቃጥሎ ንጹህ ሕሊና ይዞ ወደ ተጠራው ወደ ኤልያስ ፊቱን አዞረ:: መምሕሩ ኤልያስም ማእበል ሞገድ ማቋረጥን: እያሳየ አዕምሮውን ቀረጸው:: ያካባቢውን ሕዝብ በመንፈስ ጸንሶ በመንፈስ ለመውለድ እናትም አባትም ለመሆን ተዘጋጀ::

ሰው በቦታና በጊዜ የተወሰነ ነውና ሁሉም የተወሰነላቸውን ሩጫ ለመፈጸም የየግል ጽዋቸውን የሚጨብጡበት ጊዜው ደረሰ፥ አንድ ሳንቲም ያልነበረው ነገር ግን የመንፈስ፣ የሞራልና የእምነት ምንጭ የነበረው ኤልያስ ለሚወደው ደቀመዝሙሩ ለኤልሳዕ «ሳልለይህ አደርግልህ ዘንድ የምትሻውን ንገረኝ» አለው:: ኤልሳዕ ከመምህሩ የበለጠ የሚጠበቅበት ነገር እንዳለ የተረዳ ደቀ መዝሙር ነበረና ከመምሕሩ የፈለገው ገንዘብ፥ ሹመት፥ ክብር አልነበረም:: ይልቁንስ የሚመኘው

የመምሕሩ
መንፈስ እጽፍ ድርብ ሆኖ እንዲተላለፍለት ነበርና ይህንኑ ጠየቀው፡፡ መምሕሩ ኤልያስም «የጠየከው አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ ሆኖም ካንተ ተለይቼ በምወሰድበት ጊዜ ብታየኝ ይሆንልሐል» ነበር ያለው፡፡ ኤልሳዕም መምሕሩ ኤልያስ ሲለየው አንጋጦ እየተመለከተ «አባቴ ሆይ! ሰረገለኞችና ፈረሰኞች ሆይ» እያለ ጮኹ፤ መጀመሪያ በአጽፉ በተጠራበት ጊዜ በሬወቹን ከነ መሳሪያቸው አቃጥሎ እንደወጣ ሁሉ፥ አሁን ደግሞ የለበሰውን ቀድዶ ካረጀው አመለካከቱ ስውነቱን አላቀቆ ነጻ ካደረገ በኋላ፥ ኤልያስ ለብሱዋት የነበረችዋን ያችኑ አጽፍ ተቀበለና ለበሳት፡፡ ከዚያ በኋላ ኤልሳዕን በሩቅ ያዩ ሁሉ «ወአእረፈ መንፈሰ እግዚአብሔር ላእለ ኤልሳዕ ዘነበረ በመንፈሰ ኤልያስ» እያሉ መሰከሩ፥ ከመምሕሩ ከኤልያስ ያየውን ማእበል ሞገድ ማቋረጥ ብቻ ሳይሆን የመረረውን አጣፈጠ ምድሪቱ የተዘራባትን ፍሬ እንዳትሰጥ፥ የጸነሱ እንስሳት እንዲጨነግፉ፥ ያረገዙ እናቶች እንዲአስወርዱ እንዲያደርግ ተረግሞ የነበረውን ወንዝ ሁሉ ወደበረከትና ወደሕይወት ለወጠ፡፡ የዱር አራዊቶችን ሁሉ አዘዛቸው፡፡ ፌዘኞችን ገሰጻቸው ቀጣቸው፡፡ በዘመኑ የሚነሱት ወጣቶች በሽማግሌወች በታሪክ፥ በእምነት እንዳያፌዙ ትልቅ ተግሳጽ ጻፈባቸው፡፡ መምህሩ እንዳለው ኤልሳዕ ከመምህር ለመቀበል የጠየቀው ከባድ ቢሆንም ከመምሕሩ የተረከበውን ኃላፊነት ተወጣ፡፡ ከመምህሩ የበለጠም አደረገ፡፡

ያችን ጉባዔ ቤት የከፈቱ ታላላቅ ክቡራን አባቶቻችንና፥ ሊቃውንቱ መምሕሮቻችን ኤልያስ በኤልሳዕ ትክሻ ላይ ያስቀመጠውና የጠበቀው አይነት አደራ በኛም ላይ ጥለውብን ነበር፡፡ እኛም ብንሆን ኤልሳዕ ኃላፊነቱን በተወጣበት መንገድ ኃላፊነታችንን እንደምንወጣ በወቅቱ የጋለ መነፈስ ይታይብን ነበር፡፡ ሊቃውንት ሆይ! እስካሁን ነበር፡ ነበር፥ ነበር እያልኩ የገለጽኩት እንደኔ ሁሉ በአዳንዶቻችሁ አዕምሮ ላይ እንደሚፈላና ጊዚያዊ ረፍት ለማግኘትም ልታለቅሱ እደምትችሉም ከራሴ ተመክሮ ይገባኛል፡፡ ለምሳሌ አቡነ ቀውስጦስ የመጽሐፍ ትርጓሜ መምሕር ሆነው ከደብረ ሊባኖስ የለቀቁት መጻሕፍትን የበለጠ ለመመርመር ጥሞናው፥ ጸጥታውና ምናኔዎን ወደ በለጠውና ወደሚያመቸው ወደ ሰቃ ገዳም ነበር፡፡ «ከመነኮሳችሁ ከገዳም እንዳትወጡ፥ የተረከባችሁትን የጉባዔውን ቅርስ እዚያው ጉባያችሁን በማስፋት ለሚከተላችሁ ትውልድ ለማስተላለፍ በትምሕርቱ ላይ ጠንክሩ» ብለው የመከሩንንም ከደብረ ሊባኖስ ከወጡ በኋላ በሰቃ ገዳም ጀምረውት ነበር፡፡ እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ተመክሮ በኋላ ወደ ጽጽስናው የመጡ ከሌሎቹ በከተማ ካደጉት ሰወች በተለየና በተገቢው መንገድ በሊቃውንቱና በፍጹማን አበው እየተቀረጹ መስመሩን ጠብቀው መምጣታቸው እጅግ የሚያስደስት ነበር፡፡ ከሁለቱም ገዳማት ሲወጡ ከኤልሳዕ የበለጠ ሽክም ይዘው እንደወጡ እገምታለሁ፡፡

እኔም ከሊቃውንቱ አባቶቻችን ጉያ ከደብረ ሊባኖስ ወጥቼ  ለዘመኑ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ መምሕሮቻችን ስሰናበታቸው «ወኩሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንኡ» በሚለው በቅዱስ ጳውሎስ ቃል ሲሸኙኝ ከአይናቸው ወደኔ የተወረወረው ጨረር አሁንም ከፊቴ ላይ ያበራል፡፡ ቃላቸውም ትዝ ሲለኝ አንጀቴን ይሰብቀኛል፡፡  አባቶቼ እንደመከሩኝ ከትዳርና ሕጻናት ከማሰደግ ጋር በየደረስኩበት ከዘመኑ መምህራን አዳዲስ እውቀት ስቀስም የሐዲሱ መምህር፥ የሊቁ መምህር፡ የምሥጢር መጋቢአችን የኔታ ፍስሐና የቅኔ መምሕሮቻችንን ስሰናበታቸው የሰጡኝ የመሸኛ ምክር መላከ ብርሃን አድማሱ በመጽሐፋቸው እንደጠቀሱት መድሎት (ሚዛን) በመሆን እስካሁን ለጭንቅላቴ ታላቅ መልሕቅ ሆኖልኛል፡፡ ምንም ልማር የትም ልሂድ ይህ አባቶች በራሴ ላይ የተከሉት መልሕቅ የማየውንና የምሰማውን ሁሉ ለግል ሕይወቴ የምመዝንበትና የምለካበት ሚዛን ሆኖኛል፡፡ ሆኖም ሊቃውንቱ አባቶቻችን እንደመከሩኝ በሕግ ውስጥ በማለፍ በትዳርና ልጆች በማሰደግ ብሰማራም፥ ሕዝቡ የሚአለቅሰው ልቅሶ፥ የሚራበውን የሚጠማውንና የሚሰቃየውን ሥቃይ ባለመካፈሌ እጅግ ያሳፍረኛል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን መድሎተ አሚን የሞራል የታማኝትና የጽድቅ ሚዛን ተሰብሮ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስትዋዥቅ ሕዝቡ ግራ ሲጋባ አይና የተቀበልነው አደራ መለስ ብየ ስቃኘው እጅግ አዝናለሁ፡፡

አሁን ወደ ሰማሁትና ወዳየሁት ሁላችንንም ወደ ሚአስጨንቀን መልስ ወዳጣንለት ችግር ላይ ለማተኮር ችግሩን እየጠቃቀስኩ ወደ ጥያቄየ ስሻገር በኔ በጠያቂውና ጥያቄውን እንዲመልሱልኝ ከምሻው እንደነ አቡነ ቀውስጦስ ካሉ አባቶች ሆነ ሌሎች የሚያስከትለውን ጥላቻ፥ አሽሙርና፥ ለማፌን የሚደረገውንም ሙከራ ዘንግቼ አይደለም፡፡ በቼም ቤታችን በማይገባ ብቀላዊ ግዝት የተሞላ ሆኑዋልና የግዝትን ትርጉምና ግብር ያልተገነዘቡ ሰወች ዛሬም ሳያፍሩ እንገዝት ሊሉም ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ መንገድ የሚከተለውን ግዝት እንዳባቶቻችን የወፎች ግዝት የሚል ስም ሰጥቼ ሊያስጠይቀን ስለሚችለውና ስለሚገባው የሐላፊነት ጉዳይ ላይ በማተኮር ጥያቄየን እቀጥላለሁ፡፡ የተቀባበትን ሊጥ አብስሎ ማውጣት ያልቻለ የምጣድ ገል ያደረገን አዚም ምድነው? ከአብነት ሊቃውንት መምሕሮቻችን ጋር በነበርንበት ጊዜና ስንለያቸው ኤልሳዕ እንዳደረገው አተኩረን አልተመለከትናቸውም ነበርን? ወይስ የተቀበልናቸው ረድኤት ያለበትን አጽፋቸው ሳይሆን ሰበናቸውን ነብር? ነው አጽፋቸውን ቆብ እየሰፋን የእንጀራ መበያ ሳህን አደረግነው?  ንባቡንና ትርጓሜውን በልባችን የትርጓሜዎችን ምሥጢር በአዕምሮአችን ለመቅረጽ ቀን በጸሐይ ሌሊት በጨረቃ እንቅልፍ አጥተን፥ ኤልሳዕ ከመምሕሩ ከኤልያስ ኃላፊነቱን ሲረከብ እንደተጨነቀ፥ እኛም ከመምሕሮቻችን የሰማነውን ሁሉ ለማስቀረት ያን ሁሉ ስንሰቃይ የነበረ እንዲሁ በከንቱ ለሚቀረው ነበርን? ዛሬ እንኳን በብረት ቁልፍ የተዘጋው የነገረ መለኮቱ መግለጫ የነበረው ግዕዝ፥ የጠራው አማረኛ ከየአውደ ምሕረቱ ጨርሶ ሊጠፋ የተቃረበበት ዘመን እንደሆነ በግልጽ እያየነው ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ አውደ ምሕረት ላይ ሲነገር የሚሰማው አማረኛ ከኦርቶዶክሱ የራቀ የተለያየና የተዘበራረቀ የሃይማኖት ሽቀጥ የተሸከመ የከተማ ተረት ነው፡፡ ቋንቋው ሁሉ ተለወጠ፡፡ ሌላው ቀርቶ ወንጌሉ የሚነበብበት አውደ ምሕረቱ ተለውጦ መድረክ እየተባለ ሲጠራ እየሰማን ነው፡፡ ታዲያ ይህንን ሐብት ለመጠበቅ የተረከብነውን ሐላፊነት ከምን ጉድጉዋድ ጣልነው?

ኤልያስ ሳይመርጣቸው ወይም እንደ ኤልሳዕ ሳይሆን ባቋራጭ ለሹመቱና ለሽልማቱ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የገቡ ብዙዎቹ የመጡበት ጉዳይ ሌላ ነውና ሊፈርድባቸው አይገባም፡፡ የመጣነው ኤልያስ መርጦን ነው የምንለውስ ብንሆን ብዙ ስሕተቶች ሲፈጸሙ እያየን ዝም ብንል፥ ከሌላ ቦታ ማግኘት የማንችለውን ክብር ሳንደክምና ሳንጥር ለማግኘት

ባቋራጭ ክብርና ገንዘብ ለመሰብሰብ የተሰለፍን ምንደኞች መምሰላችን ይቀራልን? በዚያች አይነት ጉባዔ ቤት ያደግን ሰወች ምን ነካን? ምን አፈዘዘን? እነዚያ ቅዱሳን አባቶቻችን የቀረጹብን ምሥጢርና ሀላፊነት በቀላሉ ከአእምሮአችን ተፍቆ እንዴት ሊወድቅ ቻለ? መጀመሪያ ወደ ደብረሊባኖስ ወይም ሌሎች ገዳሞች ስንላክ የተጠራንባትን አጽፍ ማን ገፈፈን? ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የነበረው ሁሉ የመምሕራን ሞራል ጠፍቶ፥ በየቦታው እንደአሸን የሚፈሉትን መነኮሳት እየመለመለ ሰይሞ የሚያሰማራቸው መምሕር ምን እንደሚላቸው ባይታወቅም ልኡካን ነን የሚሉ መነኩሴዎች ስራ የአሰማሩዋቸውን ሰዎች ባህሪ እየገለጸ ነው:: አደራን ማስተላለፋና ተረክቦ መወጣት ከክርስቶስ በፊትና በሁዋላም የነበረ ነው:: የሊቃውንቱ አባት ሶቅራጥስ ይህችን ዓለም በመረረ መርዝ ሲሰናበታት ለተማሪወቹ የተናገረው ይህንኑ ነበር:: ይልቁንም የምናመልከው ጌታችን ክርስቶስም «በኔ የሚአምን እኔ የማደርገውን ያደርጋል፥ ከዚያም የበለጠ ያደርጋል» እያለ በመናገር መምሕር በተማሪወቹ ላይ ሊኖር የሚገባውን ተስፋ አጎላው:: በመንፈሳዊውም ሆነ በማነኛውም ትምህርት አቅጣጫ ካንድ መምህር የወጡ ሁሉ እንደ ይሁዳ ካሉት በቀር ባንድነት ባንድ ቦታ ባይኖሩም የተሰጣቸውን እውነት ሳይለቁ ሁሉም ስለ አንዲት እውነት በመተባበር በተለያዩ ቦታወች በሞራላቸው በእምነታቸው ቆመው በመሞት ከመምህሮቻቸው ከተቀበሉት አደራ የበለጠ ስራ እየሰሩ አለፉ:: ዓለምም በጥበብ እያበበች ከዚህ የደረሰችው ከመጀመሪያወቹ ጠበብቶች የዘመኑ ጠበብቶች የበለጠ ሐላፊነት ስለሚወስዱ ነው:: ዛሬ በአገራችን ይህ ሁሉ ተሰርዞ በቤተክርስቲያናችን እንመራለን የሚሉ ሰዎች እያመነኮሱ፥ እያቆመሱ እያጰጰሱና እያቀሰሱ ጥቁር ካባ እያለበሱ የተዛባ ትምህርት እያስታጠቁ ወደ ሕዝቡ የሚልኩት መምሕራን ምን አይነት መምሕራን ናቸው? ያባትህ ቤት ሲፈርስ አብረህ አፍርስ ከምንል ጥቂት ወገበ ነጮች አፋቸንን በዕለታዊ ዳቦ አፍነን በምቾት ከተቀመጥን ካህናት መነኮሳትና ጳጳሳት በቀር ሁሉም ግራ እየገባው ነው::

ለመሆኑ በአሁኑ ወቀት ቤተ ክርስቲያናችን ቀሳውስት፣ ቆሞሳትና መነኮሳት ብላ የምትሰይምበትን ስርአት እነ አቡነ ቀውስጦስን ያሰማራቸው ሲኖዶስ ነው የሚያዘጋጀው? ወይስ እየፈለፈለ የሚያሰራጭ ሌላ ያልታወቀ ሕቡዕ ድርጅት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ተፈጠረ? ሁሉም ቆሞስ የሚል ሹመት ተሰጠን ይላሉ:: ቆሞስ ማለትስ ምንድነው? የምንኩስናውን ምሥጢር በቅጡ አስተካከሎ ያላወቀውን ማንንም እንጀራ ሊበላ የቀረበ ቅሬ ቆሞስ እያሉ በሕዝቡ ላይ መልቀቅ ተገቢ ነውን? ብዙወቹ እንኳን ምንኩስናውን ገዳማቱን አይተው የሚያውቁ አይደሉም:: ወደውጭ የሚላኩት ሁሉ ላድርግልህ አድርግልኝ በሚል ዓለማዊ እንካ በእንካ ሸፍጥ እንደሆነ በሰፊው እየተነገረ ነው:: ምንኩስና የገንዘብ ማግኛ፣ ባዲሳበባና በሊሌሎችም ከተሞች የፎቅ መስሪያ፣ ለድብቅ እቁባቶች ማስጌጫና ወደ ምእራብ አገሮች መግቢያ ፓስፖርት እየዋለ እንደሆነ ሕዝብ እየተናገረ ነው:: ታዲያ ምንኩስና ከገዳም ወጥቶ ለእእንደዚህ አይነት ከንቱ ጉዳይ መዋሉ አያስለቅስም? ደርግ የመርካቶንና የፒያሳን ካሕናት አዘጋጅቶና አደራጅቶ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ካስወገደ ባኋላ፥ በጌታችን ትምህርት፤ በሐዋርያት ትርጉም ህግጋት፤ በሊቃውንት ካህናት ትመራ የነበረችው ቤተ ክርስቲያናችን በጓዶች እንድትመራ በማድረግ መጥፎ ጠባሳ ጥሎብን አለፈ:: እርግጥ ነው በንጉሡ ዘመንም ቢሆን ለልእልታቱ አገልጋይ ሆነው ይሰሩ የነበሩ ስልቦች በአገልግሎታቸው መጨረሻ ከቤተ መንግሥቱ ሲሸኙ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ምንም ሳይማሩ እየመነኮሱ ወደ ቤተ ክህነት የመጡ እንደነበሩ አውቃለሁ:: በግብር ሰብሳቢነት ተቀጥረው ብዙ ያገለገሉ ሠራተኞችም እንደነበሩ አስታውሳለሁ::

በየዘመኑ አንዳንድ ወገበነጮች ከመርካቶ መንገድ ተለቅመው በፖለቲካ መሪወች በኩል ሠርገው የገቡ ቢኖሩም፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቁልፍ ለሆኑ አመራሮች በሞራላቸውና በትምህርት ችሎታቸው የተመዘኑ መአስባን (በሕግ የተወሱ ካሕናትና፥ በሞራላቸውና በእውቀታቸው ሰፊ ልምዳ ያላቸው ክርስቲያኖች) እየተመረጡ ይሰየሙብት ነበር እንጂ፥ ዛሬ እንደምናየው የራሳቸውን ቆብ እየሰፉ ባጠለቁ ወንደ ላጤዎች ቤተ ክርስቲያናችን የተወረረች አልነበረችም:: (ነገሮች አጣሞ በመውሰድ እውነቱን በጫጫታ ሰውሮ ሰውን አስጠልቶ ማለፍ የተለመደ ነውና ይህን ስል ምንኩስናን የሚቃወም ነው የሚሉ ፍልስጣዎች እንዳሉ ስለማውቅ በመሠረቱ ምንኩስናን አልቃወምም:: ጥያቄየ የነ እንጦንስን መስመር ለምን ሳተ? የአሁኑ ሥርአት ከምን የመጣና ከየት የተወረሰ ነው? ቤተ ክርስቲያናችን ከተረከብነው ከተማርነውና ከቀሩት ኦርቶዶክሶች እየተለየች በመሄድ ላይ ያለችው በቅርብ እዚህ ካንሳስ(አሜሪካ) ላይ በተከሰተው ነገረ ማርያም ብቻ ሳይሆን ለሆድና ለቅንጦት ሲባል ሊቅነት፣ ሙያና ሥርአት በሐሰት ቆብ በመተካት ላይ በመሆኑም ነው:: ሕጋውያን ካሕናት እየተደመሰሱ የተማሩት ሊቃውንት እየተዘመተባቸው ነው:: መቼም ይህን ስናነሳ በዚህ መንገድ ከገቡት ሁሉ መጋጨታችን የሚቀር አይደለም:: መተዳደሪያቸው አርገውታልና:: ሆኖም እራት በዳረጎት ስለማይለወጥ አደራችንን ረስተን ራታችን ከሚቀር የነሱ ዳረጎት እንዲቀር የመምረጥ የሞራል ግዴታ ሊሰማን ይገባል::

አባቶቻችን ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያናችን በመአስባንና በደናግል እኩል ለምትወረሰዋ መንግሥተ ሰማያት ምሳሌ እንደሆነች ሁሉ አገልግሎቷም በዚያው መስመር እንዲቀጥል አስተምረውን ነበር:: ከኦርቶዶክሱ ሥርአት ዝንፍ ብለው የተጓዙት ድርጅቶች የገጠማቸው ሁሉ መዝረክረክ በኛ ቤተ ክርስቲያን እስኪከሰት ድረስ አባቶቻችን በጉባዔያቸው የሰጡንን ሐላፊነት ረስተን እኔም እናንተም የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ ሁሉ ቆመን መጠበቅ ተገቢ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያናችን የእውነተኞች ክርስቲያኖች ሁሉ ቤት መሆኗ ቀርቶ፥ በሐሰትና በማስመሰል ብቻ ከሰውነት ወደ መላእክትነት ተለወጥን ለሚሉ ከተማ እናድርጋት ተብሎ ታስቦ ከሆነም:: «ኢነስኦ ለዘነስአ እመላእክት አላ እምዘርአ አብርሃም» የሚለውን መካድ ነው:: ቤተ ክርስቲያናንን ከሕገ አውስቦ (ይቅርታ ዛሬ ሕዝባችን ወሲብ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ከመደበኛው ትርጉም አርቆ ነው) ውጭ በተወለዱ የኔፍሊሞች ከታማ በማድረግ ለከፍተኛ ውድቀት እያዘጋጀናት ነው:: (ኒፍሊሞች በሕገ አውስቦ ያልተወለዱ ዘፍ ፮: ተመልከት) የጥንት አባቶቻችን ከደብር መምሕራንና ከጠቅላይ ጽ/ ቤት እስከ ወረዳ ጽ፥ ቤት ድረስ በመነኩሳት ሳይሆን በመአስባን እንድትተዳደር ያደረጉት መነኮሳት ስላልነበሩ ነበርን? እንዲአውም «እንደ ብረት ጸንተሕ ሳትወላውል በምትናገረው ቁም» የሚሉ ሊቃውንት መነኮሳት ነበሩ:: ተወዳድረውና ደጅ ጸንተው ገጸ ጉሑሉት አቅርበው ለሹመቱ እራሳቸውን ሊአሰልፉ ቀርቶ፥ ቢታጩም እንኳ እኛ

ራሳችንን በትዳር አልፈተን፣ ልጆች ወልደን አላሳደግን ምኑን አውቀን ይህን ሐላፊነት እንቀበል በማለት ወደ ገዳማቸው ይሸሹ ነበር።

ከላይ እንዳልኩት በዚህ ፈተና ከወደቀችው ከእኛ ቤተ ክርስቲያን በቀር በቀሩት እንደ ግብጽ ባሉት እህት አብያተ ክርስቲያናት የሚታየው የአመራር ስርአት ልክ እስከ እነ አቡነ ቴዎፍሎስ ድርስ እንደነበረው ሚዛኑን የጠበቀ ነው። በነዚህ አኀት አብያተ ክርስቲያናት መነኮሳቱ ከነገረ መለኮቱ በተጨማሪ በሕክምናው በመሐንዲስነት በአስተዳደርና በተለያዩ ሙያወች የሰለጠኑ ናቸው። እኛ ግን እውቀቱ ቀርቶ በሕዝባችን ሰርጾ የኖረው ትህትናና ይሉኝታ እንኳዋን ሳይኖረን፤ በድፍረትና በትእቢት ተወጥረን፥ ልብስንና ጫማን በማሳመር ተሽሞንሙነን፤ የቅሬ ቋንቋ እየተናገርን ሕዝብን ስናታልል እንውላለን። ኤልያስን መስለው ከኖሩ አባቶቻችን የተረከብነውን አጽፍ እንደ ኤልሳዕ በመልበስ ፋንታ አሜሪካና አውሮጳ ድረስ ሳይቀር እየኀተትን የቅድስት ቤተክርስቲያናችንን ነገረ-መለኮት(ዶክትሪን)፣ ቀኖናውን፣ ባህላችንና ሌላውንም የተቀበልነውን አደራ ሁሉ በአጽፉ እየጠቀለልን ለቀበኛ ላም ስናጎርሰው እንውላለን። በዚህም ምክንያት ቤተክርስቲያናችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥታ እጁን ወደ ፈጣሪ ከዘረጋው ከደሃው ሕዝብ ይልቅ መንፈስ ቅዱስ የራቃቸውን ገዥዎችና ሌሎችንም ስግብግብ ግለሰቦች በማገልገል ላይ ትገኛለች። ሊቃውንት ሆይ! መፍትሔው ያለው ከራሳችን ነውና ራሳችንን እንፈትሽ። ሳይበቁ ለመንበረ ስልጣን አናብቃ፤ ሳንበቃም መንበረ ስልጣን ለመጋራት ሰልፍ አንያዝ። አላግባብ ስልጣን የሰጥንም ሆነ፤ የማይገባንን ስልጣን የያዝን ንስሐ እንግባ። የተረከብነውን አደራ እንጠብቅ። ኤልሳዕዎች ከመሆን አንራቅ። አሜን።

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ (asteraye@gmail.com)